# የሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግ ደረስ “ እኛና አብዮቱ ”



ግምገማ በግዛው ጌታቸው (ሻምበል)

## ደርግ፤ የደርግ አባላትና መንግሥቱ ኃ/ማርያም

እኛና አብዮቱ ከሚለው መጽሐፍ አያሌ አሳዛኝና አስገራሚ ሁኔታዎችን ለመረዳት ችለናል። ጸሐፊው እንዳለው ሳይሆን ፤ ደርግ በቅድሚያ አብዮቱን ያኮላሸና ከዚያም ሕዝቧንና ሀገሪቱን ለአስራ ሰባት አመታት ረግጦ አዘቅት ውስጥ የጨመረ አምባ ገነን ቡድን ነው። ደርግ ለምንም ለማንም የቆመ አልነበረም ለራሱ ስልጣን እንጂ። ከወታደሩ ወጥቶ ወታደሩን ጭምር የጨረሰና ያስጨረሰ ቡድን ነው።

እንዲያስተባብር በጥድፊያ የተላከው ወታደር ራሱን ደርግ ብሎ ሥልጣንን በጠመንጃ ጨበጠ። በስልጣን ቆይታው ላደረሰው ጥፋት ደሞ ፤ ተጠያቂው የወታደሩ አምባ ገነንነት እንጂ ሻምበል ፍቅረሥላሴ እንደሚለው የተራማጁና የምሁሩ አለመጣጣም አልነበረም።

ሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም ከጂጂጋ የጦር ሠራዊት ግምጃ ቤት ሃላፊነት ተነስቶ ከእነ ለገሠ አስፋው ጋር አራተኛ ክፍለጦር ዘግይቶ የተቀላቀለው ከጦሩ ተወክሎ ሳይሆን በመሪዎች ትእዛዝ ነው። በዚያን ጊዜ በአዲስ አበባ ዋናው አስተባባሪ ሟቹ ሻለቃ አጥናፉ አባተ ነበር። የክፍላቸው ጦር እንዲመለሱ ቢጠይቃቸው እንኳን፤ ሻለቃ መንግሥቱ ሌሎቹንም አሳድሞ ሁሉም እንዳይመለሱ እርስ በርስ ተማምለው አዲስ አበባ ሊቀሩ ቻሉ። የደርግ አባላቱ በዚህ አይነት አጭበርብረው ለሥልጣን የበቁ የተንኮለኞች ክምችት ነበሩ እንጂ ፍቅረሥላሴ እንደሚለው አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ጦሩና ፖሊሱ ከስህተቱ ተምሮ በደንብ የመረጣቸው የንዑስ ደርግ አባላትን ነበር ቢባል ሃቅ ነው። እነ መንግሥቱ ግን የንዑስ ደርግ አባላትን በግድያና በሹመት በታተኗቸው።

ቀደም ሲል በኃይለሥላሴ ዘመን በሀገሪቱ የነበረው የጦር ኃይል ብዛት በጠቅላላ ከአርባ ሺህ ሰው በታች ነበር። ከዚህ ውስጥ ለኤርትራ፡ ለትግራይና ለጎንደር ክፍለ ሃገራት ተመድቦ የነበረው ጦር በጠቅላላ ከ ሁለት ሺህ አይበልጥም። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ ያለ ጥናትና ምርምር በጥላቻ ተነስተው በኤርትራ የነበረውን የኮማንዲስ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ከመበተናቸው በፊት የጦር ኃይሉና ፈጥኖ ደራሹ አገሪቱን በሚገባ ይጠብቅ ነበር። ደርግ የበተነው ይህ የተጠናከረ የኮማንዲስ ፖሊስ ጦር ከእነ ትጥቁ ወዲያውኑ የሺያቢያን ጦር ተቀላቀለ። ይህ ከመሆኑ በፊት ጀነራል አማን አንዶም በደርግ ከመገደላቸው ቀደም ሲል ኤርትራ በሚገኘው የጦርና የፖሊስ ኃይል ከፍተኛ እምነት ነበራቸው። አገር ወዳዱ ጀነራል አማን ባይገደሉ ኖሮ ኢትዮጵያ አትዋረድም ፤ ኤርትራም አትገነጠልም ነበር። እነ ፍቅረሥላሴ ዋሽተው ገደሏቸው። አሁንም በመጽሐፉ ይዋሻል።

መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከእነ ዶክተር ሰናይ ልኬ ጋር ወዳጅነት ከመፈጸሙ በፊት ከሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ ጋር የጠበቀ ወዳጅነትና ምስጢር ነበራቸው። ጥቂት የደርግ አባላትን አቅፈው ሁለቱ ሊቀ መናብርትና ዋና ጸሐፊ ለመሆን ተስማምተው ነበር። ነገር ግን በመንግሥቱ ላይ የተደረገው የመግደል ሙከራና በዚሁ አጋጣሚ የፖሊስ መኮንኖችን ከሚጠላው ከዶክተር ሰናይ ልኬና ከሕዝብ አደራጅ ጽ/ቤት ጋር የመንግሥቱ የጠነከረ ወዳጅነት መፍጠር፤ ቤተ መንግሥቱንም የሚጠብቁትን ወታደሮች ከሐረር ካስመጣና በራሱ ቁጥጥር ሥር ካደረገ በኋላ ሻምበል ዓለማየሁን ጣል ጣል ማድረግ ጀመረ ወዳጅነታቸውም ሻከረ። ይህ በዚህ እንዳለ ፤ የኢሕአፓ ድርጅት ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ወታደሩ ፀጥታ ማስከበርና የሀገር ዳር ድንበር ማስጠበቅ ስላለበት ወደ ካምፑ ይመለስ የሚል ጥያቄ ስላቀረበ ደርግና መንግሥቱ ኃ/ማርያም ጥያቄውን አልወደዱትም። ሻምበል ዓለማየሁና ሻምበል ሞገስ እንዲሁም ሌሎች ጥቂቶች የደርግ አባላት የተራማጆች አንድነት መፈጠር አለበት የሚል ሀሳብ አቀረቡ። መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሥልጣን የሚያጣ መሆኑን ስለ ተገነዘበ ሻምበል ዓለማየሁን በውጭ ለማስገደል ብዙ ሙከራ አደረገ። ሻምበል ዓለማየሁም እንዳይገደል ሌሊት ሌላ ቤት እያደረ ይሰወር ነበር። ሁላችንም አንድ ቀን እንደሚገደል እናምን ነበር። እንደተባለውና እንደተፈራው ጥር 26 ቀን 1969 ኮሎኔል መንግሥቱ፤ ኮሎኔል ተስፋዬ፤ ለገሠ አስፋው፤ፒቲ ኦፊሰር ታምራት ጠዋት በደርግ ቡና ቤት ያለወትሮአቸው በአንድነት ሆነው ሲወያዩ ሲታይ ከባድ ጥፋት ለማድረስ እንደተዘጋጁ ያስታውቅ ነበር።ነገር ግን በምንም አይነት የደርግ አባሎችንና ጀነራል ተፈሪ በንቲን ይገድላሉ ብለን አላሰብንም። ሟቾቹም ሠላምና ጤና ነው ብለው ወደ ቢሮአቸው ሲገቡ እኛም ሰላም ብለናቸው ለመጨረሻ ጊዜ ተለያየናቸው። ጀኔራል ተፈሪ በንቲ ፤ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ፤ ሻምበል ሞገስ ፤ ሌ/ኮሎኔል አሥራት፤ ሌ/ኮሎኔል ሕሩይ፤ ሻምበል ተፈራ ፤ የአስር አለቃ ኃይሉ በላይ ከስብሰባ አዳራሽ ተወስደው ተገደሉ። ግድያውን በፈጸመ ማግስት ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ " ምሣ ሊያደርጉን ያሰቡትን ቁርስ አደረግናቸው " ሲል ዋሸም ፎከረም። ነገር ግን እነ ሻምበል ዓለማየሁና እነ ሻምበል ሞገስ በምንም አይነት መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ እቅድ አልነበራቸውም ። በእርግጥ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ሥልጣኑንም ገንዘቡንም ስለሚያዝበት አምባ ገነን የመሆን ደረጃ ላይ ነበር። ሆኖም ለውጥ ካስፈለገ በሕግ እንጂ በግድያ መሆን የለበትም የሚል አቋም እነ ሻምበል ዓለማየሁ እንደነበራቸው በግል እኔ አውቃለሁ። በሃሰት እንደተለመደው የንጹህ ሰዎች ደም እንደገና ፈሰሰ።

ደርግና መንግሥቱ ኃይለማሪያም የኢትዮጵያን የጦር ኃይል ሊመሩት ብቃት የነበራቸውን ጀነራሎች በመረሸን ፤ ያልሰለጠነና ያልተዘጋጀ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን ጦር እነ ለገሠ አስፋው እንዲመሩት ተደርጎ እንዲበተንና እንዲዋረድ አደረጉት። ቀደም ሲል በኃይለሥላሴ ዘመን በኮንጎና በኮሪያ የተደነቀውና የተመሰከረለት ወታደር በደርግ ዘመን በሀገር ውስጥ ፀጥታ ማስከበር አልቻለም። ፍቅረሥላሴ በመጽሐፋ አሁንም ለድክመታቸው ኢሕአፓን ያማርራል። በእኔ በኩል ደርግ ለጥፋት የተፈጠረ የካንሰር በሽታ ነበር። ይህ የተላላፊ በሽታ ኢትዮጵያ እንድትዋረድና ግዛቷን እንድታጣ ህመም ሆኖባት በቀላሉ በወያኔ እጅ እንድትወድቅ አደረጋት።

## <u>ደርግና ኢሕአፓ፤ መኤሶን፤ ወዝ ሊግ፤ ማሌሪድ፤ ኢጭአት</u>

በአብዛኛው የመጽሐፉ ድርሰት የሚያተኩረው በኢሕአፓ ድርጅትና በኢሕአፓ አባላት ላይ ነው። ለደርግ ድክመትና ጭካኔ ሁሉ ፤እስከካሬ ድረስ ምክንያታቸው በ 1969 ዓ ም የፈጁትን ኢሕአፓን ነው ። እንደገና አሁንም እንደገና መልሶ መላልሶ በማንሳት አስራ ሰባት ዓመት ሙሉ በግዛት ዘመናቸው በቅዠት ተኝተው የሚያ ውቁ አይመስሉም። በፍቅረሥላሴ አባባል ጥያቄ ያቀረቡ ጀኔራሎች፣ የተገደሉት ሚኒስትሮች፣ ድሃ ገበሬዎች፣ በርበሬ ነጋዴዎች፣ ተቀዋሚ የደርግ አባላት ፡ ተማሪዎች አስተማሪዎች ሌሎችም ሁሉ የኢሕአፓ አባል ነበሩ ይላል። በዚህም ምክንያት ብዙ ሺህ ተራማጆችና ሀገር ወዳዶች መገደላቸውን ያረጋግጣል። በግድያዎቹ

ውሳኔዎች ላይ ተሳታፊነቱን እንደ ጀግንነት ይቆጥረዋል። በተለይ በቀይ ሽብር ዋና ተዋናይ እንደ ነበረ መታወቁ ንዴታችንን ያበዛዋል።

በ ሻምበል ፍቅረሥላሴ አባባል ኢሕአፓንና ደጋፊዎቹን በሜኤሶን ረዳትነት ከገደሉና ካሠሩ ከጥቂት ጊዜአት በኋላ፤ አብረው ከደርግ ጎን ለጥፋት ይተባበሩ የነበሩትን የመኤሶን ታጋዮችንና ደጋፊዎቻቸውን ከእየመሥሪያ ቤቶች፡ ከገበሬ ማሕበራት፡ ከወሊጋ፡ ከሸዋ፡ ከጂማ፡ ከአዲስ አበባ ከሌሎችም ጭምር እየሰበሰቡ፡ የሜኤሶን አባላት ናቸው የተባሉትን ምሁሮች፤ ወጣቶች፤ወታደሮች፤ ገበሬዎች፤ በሙሉ ፈጇቸው። የተቀሩትን አሰሯቸው። የመኤሶን መሪና የደርግ ወዳጅ የነበረውን ኋይሌ ፊዳን ሳይቀር አስረው ወስደው አሰቃይተው ገደሉት። መኤሶን ደርግን ተገን አድርጎ አባላቱን ማብዛቱንና በሥልጣን መስፋፋቱን ደርግን አስደነጦት ነበርና ምክንያት ተፈልጎ ፤ ***በሱማሌ ጦር ተወጥረን ሳለን በሱማሌ ላይ ልናደርግ ያሰብነውን ጦርነት ስለ ተቃወሙንና ስለ ካዱን ደምስሰናቸዋል*** በማለት በወቅቱ የደርግ ውሳኔ ላይ ተባባሪ እንደ ነበረ ይገልጻል።

የፍቅረሥላሴና የደርግ ጭካኔና ግድያ በኢሕአፓና በሜኤሶን ብቻ አላቆመም። እንደገና መኤሶንን ካጠፉ ከጥቂት ወራት ብኋላ ወዝ ሊግ የሚባለውን በዶክተር ሰናይ ልኬ የተቋቋመውንና የደርግ ደጋፊ የነበረውን የፖለቲካ ድርጅት ፤ በድርጅት ላይ ሌላ ድርጅት ተቀላቅላችኋል ደርግን ለማጥፋት አሲራችኋል በሚል ፤ አንገታቸውን ደፍተው ይታገሉ የነበሩትን ተራማጅና ምሁር የነበሩትን የአየር ኋይል፡ የፖሊስና የጦር ሠራዊት መኮንኖችን ፈጇቸው።

ከላይ የተመለከቱትን ድርጅቶችን አባላት ከደመሰሱ በኋላ ባላቸው የሰው ማጥፋት ልማድ፤ አብረዋቸው ይረዷቸው የነበሩትን ማሌሪድ የተባለውን በተስፋዬ መኮንን የሚመራውንና ኢጭአት የተባለውን የኦሮሞንና የደቡብ ብሔሮችን ያቀፈ ድርጅት፤ ሁለቱንም ድርጅቶች በተለያዩ ጊዚያቶች አባሎቻቸውንና ደጋፊዮቻቸውን ገደለ ብዙዎቹንም አሠረ። ድርግ በግዛት ዘመኑ በመንግሥቱ ኃይለማርያምና በእነ ፍቅረሥላሴ ወግደረስ እየተመራ የሀገሪቱን ምሑራንና ተራማጆችን መደምሰስ ብቻ ሳይሆን ፤ የሀገሪቱን ሕዝብ ወኔና የሀገር ፍቅር ስሜት ያጠፋና የሰለበ፡ ሕዝቡን ለስደትና ለመከራ የዳረገ ወንበዴ መንግሥት ነው። የሚያሳዝነው ግን ሻምበል ፍቅረሥላሴ አሁንም ደርግ በሕዝቦችና በተራማጆች ላይ የተፈጸመውን ግድያ አድናቂና ደጋፊ መሆኑ ነው። አንድም ወቅት ጸጸት አልተሰማውም። ይህ ግለሰብ አሁን ም ከስህተቱ አልተማረም።

**<u>ሻምበል ፍቅረሥላሴ ስለ ትግራይ ሓርነት ግንባር —ሕውሓት</u>**

ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ በሌሎች ድርጅቶች ላይ እንደጻፈው ሁሉ ስለ ሕውሓት ንቅናቄና ድርጅት ጽፏል። ስለ ወያኔዎች እንዲህ ሲል ይቀጥላል ። ”………………..የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘርና በጎሳ በመለያየትና፤ ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ከዓለም ካርታ ለመደምሰስ …………………..የብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል መታወቅ አለበት የሚለውን መርዘኛና በታኝ አመለካከት የቀሰቀሰው የጠባብ ብሔረተኛነት ስሜት …………. የኤርትራዊያንን ፍላጎት ለማሟላት ዋና ተዋናይ ሆኑ……………” ይላል።

ሻምበል ፍቅረሥላሴ በዚህ ብቻ አላበቃም ። በ 1969 ዓም በሕውሓትና በሱማሌ መንግሥት መካከል ስለ ነበረው ግንኙነት እንዲህ ሲል በገጽ 367 ጽፏል። “ ……………… ኢትዮጵያን ከሚወጉ ከኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖችና ከትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ( ሕውሓት) ጋር……………………….ኢትዮጵያን ለማጥፋት እቅድ ተነደፈ።…………….ኢትዮጵያን ለማፍረስ ዓላማ አድርገው የሚንቀሳቀሱት ከሃዲ ድርጅቶች በአንድነትና በተቀነባበረ ስልት ………………ትግራይን ከኢትዮጵያ ገንጥሎ ነፃ የትግሬ መንግሥት ለመመስረት ……………….የሕውሓት መሪ መለስ ዜናዊንና………………………..ሞቃዲሾ ሰብስቦ መመሪያ

ሰጣቸው..............”። እንግዲህ ይህ አባባል የሱማሌ መሪ የሳይድ ባሬንና የሕውሓትን ትብብር ለማሳየት መሞከሩ ነው።

የመጽሐፉ ደራሲ አሁንም ስለ ሕውሓት በገጽ 419 የፃፈውን እንመለከታለን ። ” ................ሕውሓት አካባቢውን በያዘበት ጊዜ የጣና በለስ ፕሮጀክትን እንዳልሆነ አድርጎ አፈራረሰው...................የግንባታና የእርሻ መሳሪያዎችን በሙሉ እየጫነ ........................ አጓጓዘ ................እየነቀለ ወሰደ ..................ነቃቅሎ አጓጓዘ በኢትዮጵያ ላይ ከጠላቶቿ ጋር በመተባበር ታላቅ ወንጀል ፈጸመ። “ በማለት ሕውሓትን ይወነጅላል። በዚህ ጉዳይ ላይ ሕውሓቶች ምን ይሉ ይሆን ?

***<u>የእነ ሻምበል ፍቅረ ሥላሴ ከእስር መፈታት፤</u>***

በአንድ ወቅት መካሪ የሌለው መንግሥቱ ኃይለማርያም በአደባባይ ጠርሙስ እየሰበረ ሲፎክር “ ፉከራ እንደ መንግሥቱ” እየተባለ ይቀለድ ነበር ። አለባበሰ እንደ ፍቅረሥላሴ ወግ ደረስ ተብሎ እንደነበረው ማለቴ ነው። እውነትም ፍቅረሥላሴ አለባበሱን ከማሳመርና በግድያ ወቅት እጁን በማውጣት ከመደገፍ በስተቀር ፈሪና አድርባይ የደርግ አባል ነበር። ይህም ዛሬም በራሱ መጽሐፍ ሳይቀር ይነበባል። **ኮሎኔል መንግሥቱ ይገሉኛል ብዬ ፈርቼ ነበር** ብሏል። የደርግ አባላት ከየቦታው የተሰበሰቡ ስለሆኑ ጠባያቸውና ግብራቸው የተለያየ ነው። አብዛኛው ያልተማረና መኪና መንዳት የማይችል ነበር። እነሱን ለማስተማር ብዙ መኪናዎች ከጥቅም ውጭ ውለዋል። መኪናና ጥሩ ጫማ ወይም ልብስ ሲያሰፈልጋቸው በደርጉ የእስረኛ ጉዳይ ኮሚቴ አማካይነት ሰዎች ታስረው መኪናቸውንና ልብሶቻቸውን ይከፋፈሉት ነበር።

ሻምበል ፍቅረሥላሴ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱን አፍቃሪ ነው። ንጉሡ ሲታነቁ ፤ ሚኒስትሮች ፤ ጀኔራሎች፤ መሳፍንቶች፤ አርበኞች፤ ምሁራን ፤ በደርግ ሲገደሉ፤ እጁን ወደ ላይ እያወጣ በህብረት ከገደሉትና በግልም የማይወዳቸውን ያስገደለ የደርግ አባል ነው። እሱና ግብረአበሮቹ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በፈፀሙት የግፍና የእልቂት ወንጀል በማስረጃ ተረጋግጦ የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ሳለ ፤ ወደ እድሜ ልክ እንዲቀየር ተደረገ። የሚገርመው ነገር አሁን በቅርቡ ሁሉም የደርግ አባላት በምሕረት ነፃ ተለቀው ይገኛሉ። የእነሱን በነፃ መለቀቅ የሚች ዘመዶች ይህን ግፍ በመረረ ሀዘን ያዩታል ። እነዚህ ወንጀለኞች በደም ባጥለቀለቁት በአዲስ አበባ መንገዶች ላይ በነፃነት ሲዘዋወሩ ማየት በጣም ያሳዝናል። ስንት ጀግኖች ቤት አጥተው እርዳታ ተነፍጓቸው በ ረሃብ ላይ ሲገኙ፤ እነዚህ ወንጀለኞች እነ ሻምበል ፍቅረሥላሴና ግብረ አበሮቹ ቤትና ንብረታቸው ተመልሶላቸዋል። ጡረታቸውም ተከብሮ ይገኛል። ምናልባትም ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ በስደት የሚያኖረውን በቂ ገንዘብ ለራሱ ዘርፎ ከኢትዮጵያ ከመኮብለሉ በፊት ወይም በኋላ ለእነዚህ የደርግ አባላት ወይም ለዘመዶቻቸው ችሮታ ያደረገላቸው ይመስላል። የጀርመኑ ሂትለርና የናዚ መሪዎችና ወታደሮች እንዲሁም ግብረ አበሮቻቸው እየታደኑ እስከዛሬ ለፍርድ ይቀርባሉ። ብዙዎቹ ናዚዎች የሞት ፍርድ ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል። ነገር ግን የኢትዮጵያዊያን ንፁህ ደም እንደ ደም አልተቆጠረም ። አሁን በዚህ ዘመን የምናየውንና የምንሰማውን ለማመን አቅቶናል።

እኔ ከፍቅረሥላሴ መጽሐፍ መማር የቻልኩት፤ ማንም ሰው መጽሐፍ መጻፍ እንደሚችል ነው። ላጠፉት የሰው ነፍስ በፍርድ የተገደሉት የናዚና የፋሽስት መሪዎች በነፃ ቢለቀቁ ኖሮ ” እኛና ሂትለር“ ወይም ” እኛና ሙሶሎኒ ” በሚል አርእስት ይጽፉ ነበር ማለት ነው። ነገር ግን በአውሮፓ ውስጥ የሂትለርን ወይም የናዚን ሥም ወይም አርማ በጋዜጣ ወይም በመጽሐፍ ማውጣት አይቻልም ክልክል ነው።

በኢትዮጵያ አያሌ ጀኔራሎችን፤ ሚኒስትሮችን፤ በርካታ ምሑራንን ፤ ተርማጆችን፤ ወታደሮችን፤ ሀገር ወዳዶችን፤ ወዝአደሮችን፤ አርሶ አደሮችን፤ ህፃናትን፤ አባትና እናቶችን፤ ወጣቶችንና ሌሎችንም ጭምር ያለፍርድ እስር ቤት በማጎር ፤በኤሌክትሪክ መጥበስና በዱላ መደብደብ ብቻ ሳይሆን ፤በሰው ዘር ላይ በተለይ በኢትዮጵያዊ ወገንህ ላይ ሊፈጸም የማይገባውን የእስረኞችን ጥፍር እያወላቁ፤ ብልታቸውን እየቀጠቀጡ፤ ዓይናቸውን እያወጡ፤ ምላሳቸውን እየቆረጡ፤ ጥርሳቸውን እየሰበሩ፤ ሥጋቸውን እየቆረጡ አሰቃይተው ይገድሏቸው ነበር። ይህንን አይነት አሰቃቂ ወንጀል የፈጸሙና ያዘዙ ወንጀለኞች በሕግ የመጨረሻው የፍርድ ቅጣት ሊፈጸምባቸው ሲገባ ለጥቂት ዓመታት ታስርው ነፃ መውጣታቸውን በሀዘን እንመለከታለን። አሁን በኢትዮጵያ በአገዛዝ ላይ ያለው መንግሥት የተፈጸመውን ግድያና ፍጅት ለይምሰል በቃል እያወገዘ በግብር ጠንካራ ሕጋዊ እርምጃ ባለመውሰዱ በታሪክ ያስጠይቀዋል። አዎ ! የደርግ መፈጠርና የኢትዮጵያ መዳከም ለኤርትራ ነፃ አውጭ ድርጅት በተለይ ደካማ ለነበረው ለሺአቢያ የኢሳያስ አፈወርቂ ቡድን መጠናከርና ለወያኔ ሕውሓት መፈጠር ምክንያት ነው። በእርግጥ ለዚህ ላበቃቸው ደርግ ውለታ መመለስ ከሆነ ያሳዝናል።

ደርግ በሀገራችን ኢትዮጵያና በሕዝቦቿ ላይ የፈጸመው ግፍና ግድያ ወደፊት ለታሪክ ግንዛቤና ለትምሕርት ከሚሆነን በስተቀር ተዘርዝሮ አያልቅም ። በጣም የሚያሳዝነኝ ግን ሕዝባችንን ፈሪና ተጠራጣሪ ፤ እርስ በርሱም እንዳይመካከርና እንዳይተማመን አድርጎት ለኢሕአደግ አሳልፎ መስጠቱ ነው።

በእኔ በኩል ደርግም ሆነ ወያኔ ሕውሓት ወዳጆቼ አይደሉም ። የሚከተለውን ያንቡልኝ።

እኛ ከፊት ለፊት መንግሥቱ ተከታይ፤

ከአሲንባም ተባረርኩ መለስ ብዬ እንዳላይ።

በዱላ በጥይት እያስፈራራችሁ፤

በሉ ተጫወቱ እንደፈለጋችሁ፤

አዋጉት እርስ በርስ ክልል ከልላችሁ።

የዛ ትውልድ ሰው ነኝ የመከረኛው፤

በስደት የምገኝ የሰው ሀገር ስው።

ግዛው ጌታቸው ( ሻም )

<u>ማስታወሻ</u>

ሻምበል ግዛው ገድሉ የአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ነ0ኛ ኮርስ ምሩቅ ሲሆኑ በተለያየ የፖሊስ ሰራዊት ውስጥ በሃላፊነት ከማገልገላቸውም በላይ በደርግ ዘመነ መንግሥት የንኡስ ደርግ አባል ሆነው የታገሉ የደርግን አምባገነንነት ተቃውመው በትግል ሜዳ የተዋጉ ዛሬ በስደት የሚኖሩ መኮንን ናቸው።